# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# አርባ አመታት

ጸሐፊው: Edward Hughes
የተተረጎመው: Abel Eshetu
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen

ታሪክ 12 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

አማርኛ

Amharic



እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ባወጣቸው ጊዜ ሙሴ የሕዝቡን አምልኮ ይመራ ነበር። የምስጋና መዝሙር አዘጋጅቶም ነበር። “በክብር ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ” ብሎ ዘምሯል። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ስላደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ሙሴ መዝሙር ተቀኝቷል።




1



እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ ሶስት ቀናት ከተጓዙ በኋላ ተጠምተው ነበርና አንድ ምንጭ አገኙ። ነገር ግን ውሀው መራራ ስለነበር መጠጣት አልቻሉም። ከመፀለይ ይልቅ ሕዝቡ አጉረመረሙ።



ነገር ግን እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለሆነ ውሀውን ፈወሰው።

2



ሕዝቡ በሁሉ ነገር ያጉረመርሙ ነበር። በግብጽ እያለን የሚበላ ምግብ ነበረን፤ በዚህ ምድረ በዳ ግን በረሃብ ልናልቅ ነው ብለው ጮሁ። በዚያ ምሽት እግዚአብሔር ድርጭት ላከላቸው። እነርሱም ያዟቸው።

3

በነጋታው ጠዋት ደግሞ መና ላከላቸው። መና ልክ እንደ ዳቦ የሚጣፍጥ ምግብ ነው።



በየማለዳው መና መሬት ላይ ይገኝ ነበር። እንዲህ ባለ መልኩ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምድር በዳ ይመግባቸው ነበር።

4

በየዕለቱ የሚበቃቸውን ምግብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኙ ነበር። አንዳንዶች ግን ከሚበቃቸው በላይ ለነገ ብለው መና ቢሰበስቡም ይበሰብስባቸው ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለነገ ብለው ትርፍ እንዳይለቅሙ አዞአቸው ነበርና።



5

ለነገ ብለው የሰበሰቡት ሁሉ ትል ያወጣ ነበር። በነገታው ሰንበት ሲሆን ብቻ ነበር ለነገ ብለው መና እንዲለቅሙ ያዘዛቸው። ነገ ሰንበት ሳይሆን የለቀሙት ሁሉ ግን ይተላ፤ይሸትም ነበር።



6

እግዚአብሔር እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሲጓዙ ይንከባከባቸው ነበር። ምግብና ውሀ ይሰጣቸው፤ከጠላቶቻቸውም ያድናቸው ነበር።

እስራኤላውያን ከአማሌቃውያን ጋር ሲዋጉ ሙሴ በትሩን ወደ ላይ ሲያነሳ ያሸንፉ ነበር።



7



እግዚአብሔር እስራኤላውያንን “ትዕዛዛቴን ብትጠብቁ ለእኔ የተለያችሁ ሕዝብ ትሆናላችሁ” አላቸው። እነርሱም ለሙሴ “እግዚአብሔር ያለንን ሁሉ እንታዘዛለን” አሉ። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በሲና ተራራ እየተነጋገረ ሳለ በተራራው ስር ሆነው ይጠባበቁት ነበር።

8



ሙሴም በተራራው
ላይ አርባ ቀናት
ከእግዚአብሔር
ጋር ቆየ።
እግዚአብሔርም
አስሩን ትዕዛዛት
በድንጋይ ጽላት
ላይ ጽፎ ለሙሴ
ሰጠው። ሕጉም
እስራኤላውያን
የሚተዳደሩበት
መመሪያ ነበር።

9




10




11



ከእግዚአብሔር ጋር
እያለ እስራኤላውያን
አንድ አሳዛኝ ነገር
አደረጉ። አሮን ከወርቅ
ጥጃ እንዲሰራላቸው
አደረጉና በእግዚአብሔር
ፋንታ ያመልኩት
ጀመር። ከዚህም የተነሳ
እግዚአብሔር እጅግ
ተቆጣ። ሙሴም
ተበሳጨ።

12



ሙሴ ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ
የወርቅ ጥጃውንም
ዘፈኑንም አየ፤ የሙሴም
ቊጣ ነደደ፥ ጽላቶቹንም
ከእጁ ጥሎ ከተራራው
በታች ሰበራቸው።
የሠሩትንም ጥጃ ወስዶ
በእሳት አቀለጠው፥ ጥጃውን
ያመለኩትን ሁሉ በሰይፍ
ገደላቸው።

13

እግዚአብሔር ለሙሴ ሌላ
ሁለት ጽላቶች ሰጠው። ከዚያም
የመገናኛ ድንኳን እንዲሰራ
አዘዘው። ይህም አጥር ያለው ትልቅ
ድንኳን ሲሆን እግዚአብሔር በሕዝቡ
መካከል የሚያድርበት ነው። ሕዝቡም
በዚያ እግዚአብሔርን ያመልካሉ።
የደመናና እሳት አምድ
የእግዚአብሔርን
ከሕዝቡ ጋር መሆን
ያሳይ ነበር።





14

ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት በተቃረቡ ጊዜ ሙሴ ምድሪቷን እንዲሰልሉ አስራ ሁለት ሰዎችን ላከ። እነርሱም ምድሪቷ ምቹ እንደሆነች ተናገሩ። የምድሪቷንም ፍሬ ይዘው ለሙሴ አመጡ። ኢያሱና ካሌብ ደግሞ በእግዚአብሔር እርዳታ ምድሪቷን እንደሚወርሱ አምነው ተናገሩ።



15

ሌሎቹ አስር ሰላዮች ደግሞ የምድሪቷን ጽኑ መሆንና የሰዎቹን ረጃጅምነት አይተው ስለፈሩ “እኛ ምድሪቷን መውረስ አንችልም” ብለው አጉረመረሙ።

እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር ሲያወጣቸው ያደረገውን ተዓምራት ሁሉ ረስተው ነበር።



16

ሕዝቡ አስሩ ሰላዮች ያሉትን አምነው ስለፈሩ መጬህ ጀመሩ። ወደ ግብጽ ምድርም ለመመለስ ፈለጉ። ሙሴንም ሊገድሉት ፈለጉ።



17

እግዚአብሔር ግን ሙሴን አዳነው። ሕዝቡንም “በዚህ ምድር በዳ አርባ አመታትን ትንከራተታላችሁ፤ ኢያሱና ካሌብ እንዲሁም ልጆቻችሁ ግን ወደ ተሰፋይቱ ምድር ይገባሉ፤ ይወርሳሉ” አላቸው።



18

አርባ አመታት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 15
እስከ ዘሌዋውያን ምዕ. 14

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣ ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16